# *የአማራው ሕዝብ ከፄት ወዴት*

**መጽሐፍ ደራሲ - አንጻርጋቸው ጽጌ**

**ሒስ - ጌታቸው ኃይሌ (ከሚኒሶታ)**

(ከዚህ በታች ያለው ሒስ *ምረሽ* ቅጽ 2 ቍጥር 2 (1986) ከወጣው ላይ የተቀዳ ነው።)

ይህቺ በትልቅ ሰው መዳፍ የምትሸፈን ባለ 62 ገጽ መጽሐፍ የታተመችው አዲስ አበባ ሰኔ 1985 ዓ. ም. በቦሌ ማተሚያ ድርጅት ነው። በዚች መጽሐፍ አማካይነት ደራሲው "ለአማራው" ሕዝብ የሚያስተላልፈው መልእክት፥ እኛ አማሮች በጎሳችን በፖለቲካ ተደራጅተን የወያኔ መንግሥት ከኢትዮጵያ ምድር ላይ መጥኖ በዳረገን ክልል ተወስነን እንኑር የሚል ነው። ስለዚች መጽሐፍ (ስለደራሲው ማንነትና ስለድርሰቷ መልእክት) በዝርዝሩ ለማወቅ የፈለገ ከዚህ ቀደም ብዙዎች የተቹትን (ለምሳሌ አቶ ሰውነት መልካሙ በ*ጦቢያ* ሐምሌ 1985፥ ገጽ 43-45 ላይ ያሳተመውንና ደራሲው ተጨማሪ አስተሳሰቡን በ*ማኅሌት* ሐምሌ 1985፥ ገጽ 192-23 ያካፈለንን) ማንበብ ይበቃል።

የኔን ብዕር ያከልኩበት በሁለት ምክንያት ነው። አንደኛ፥ ይኸንን አጋጣሚ ምክንያት በማድረግ ስለብሔርተኝነት (ስለጎሰኝነት) ያሉኝን አንዳንድ ሐሳቦች ለማጠቃለል ሲሆን ሁለተኛ፥ የዚችን መጽሐፍ ሐሳብ ከሚደግፉና ከሚከተሉት አንዱ በ*ኢትዮፒያን ሪቪው* (October 1993, ገጽ 56-58) የጻፈውን ጥሪ ስላነበብኩ ጥሪውን ማክበር እንደማይገባ ለማሳየት ነው።

አንድ የጎሳ ፖለቲካን አጥብቆ የሚጠላ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅትን (መአሕድን) ግን አጥብቆ የሚደግፍ ሰው ስልክ ደውሎ እነዚህን ጽሑፎች (*የአማራው ሕዝብ ከፄት ወዴት* የሚለውንና በ*ኢትዮፒያን ሪቪው* ላይ የወጣውን "የአማራውን መደራጀት ኢትዮጵያን ከመበተን ጋር ምን አያያዘው" የሚለውን) አደነቀልኝ። መአሕድን ሊተኩ ወይም መንገዱን ሊያጥፉ (ሊቀለብሱ) የሚዶልቱትንና መአሕድን ባንድነት እንዴት እኩል ማድነቅ ይቻላል? እነዚህ ሰዎች ኤርትራ ስትሄድ፥ ሌሎችም እንዲሄዱ መንግሥት ሲገፋፋቸው ዓይናቸው እያየ፥ "ሀገር ተበተነ የሚለውን ከታሪክ አንጻር ስንመለከት የምንማረው ሀገሪቱ በማንም ኃይል እንደማትበተን ነው" የሚሉ ናቸው። ታዲያ መአሕድንና እነሱን ምን አንድ አደረጋቸው? ሁለቱ እንደቀንና እንደሌሊት የተለያዩ ከሆኑ "መኑ ዘደመሮ ለመዓልት ምስለ ሌሊት?" ባጭሩ የጎሳ ፖለቲካን ለመቃወም የተቋቋመውን መአሕድንና እነዚህን የጎሳን ፖለቲካ ለመደገፍ የሚሯሯጡትን ለይቶ ማየት እንዴት ያቅታል? (ዱባና ቅል ለየቅል።) የበግ ደበሎ የለበሰ ሁሉ በግ አይደለም። የአማርኛ ተናጋሪውን ጠላት አልፎ አልፎ በመዝለፍና ያዘኑለት ለመምሰል "ደበሎ ለባሽ" በማለት ብቻ የአማርኛ ተናጋሪውን ሕዝብ ወጥመድ ማስገባት አይቻልም።

**ትርፍ የለውም፤**

ካነበብኳቸውና ከተቸኳቸው መጻሕፍት ሁሉ እንደዚች መጽሐፍ እየተሙለጨለጨ ያስቸገረኝ አንድም አላጋጠመኝም። ይኸም የሚሆነው ደራሲው የራሱን አዎንታ በራሱ አሉታ ስለሚደመስሰው ነው። አንዱ በሌላው ከተደመሰሰ በመጨረሻ ምን ይተርፋል? አንድ ሰው አንድ ቍጥር ሰጥቶ ያንኑ ያህል ቍጥር ቀንሱለት ቢለንና ብንቀንስለት ምን ያህል ይቀርልናል? በደራሲው አጻጻፍ ቍጥሩ ያንኑ ያህል ተቀንሶለት ምንም አይጐድለውም! ለምሳሌ ገጽ 15 ላይ "በተለይ የተለያዩ ብሄርና ብሄረሰቦችን አስገብረው የዛሬይቱን ኢትዮጵያ የመሰረቱት የሸዋ ነገሥታትና መሳፍንት የግዛታቸውን አንድነት ለማስጠበቅ ከተጠቀሙበት ስልቶች አንዱ ልጆቻቸውን ለተለያዩ ብሄሮች መሳፍንትና ባላባት ልጆች መዳር ነበር" ይላል። ይኸን ሳነብ በጋብቻ አማካይነት ዝምድናና ሰላም መፍጠር የሚደነቅ ከመሆኑም በላይ በሸዋ ነገሥታትና መሳፍንት የተጀመረ ዘዴ አለመሆኑን ለማሳየት ፈለግሁ። ግን ይኸንን እንዴት አድርጌ ልናገረው? ማስረጃ

ልፈልግ ስል፥ ደራሲው ተሽቀዳድሞ እዚያው ገጽ ላይ "ይህ አሠራር በመካከለኛው ዘመንም በአውሮፓ ነገሥታት የተፈጸመ ከቅድመ ምኒሊክ (= ምኒልክ) በፊትም በሰሜን ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የተለመደ አሠራር ነበረ" ይላል። ይኽ ሊገርመኝ ራሱ ያፈረሰውን እንዳልፈረሰ ለመንቀፍ ሲገሠግሥ ለማስረጃ የሚሰጠው ምሳሌ "የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሳ መለያየትን አያውቅም? የሚሉ ወገኖች ለሐሳባቸው ማስረጃ የሚሰጡትን ነው። እንዲህ ይላል፦

> አፄ ሃይለ ሥላሴን ብቻ እንኳን ብንወስድ፥ ልጆቻቸውንና የልጅ ልጆቻቸውን ከአምስት ላላነሱ የተለያዩ ብሔር መሳፍንትና ባላባት ልጆች ድረዋል። እንግዲህ ከማሳፍንቱም፥ ከመኳንንቱም፥ ከምሁሩም፥ ከነጋዴውም፥ ከአርሶ አደሩም በዚህ ዓይነት የጋብቻ ትስስር የገቡ እንዳሉ ግልፅ ነው።

ሌላ ምሳሌ ለመጨመር፥ ደራሲው አማራ የሚባል ብሔረሰብ የለም የሚሉትን በጥብቅ ይነቅፍና ገጽ 22 ሲደርስ ". . . በዘመናዊት ኢትዮጵያ ሃገር ምስረታ ግምባር ቀደም ሚና የተጫወተው ጠንካራ የሆነ የተማዕከለ አስተዳደር የነበረው የራሱን ብሔረተኝነት በዚሁ አስተዳደር አማካይነት ያዳበረ አማራ የሚባል ብሄር አልነበረም" ይለናል።

ደራሲው አማራ ማለት ክርስቲያን ማለት እንጂ የሕዝብ መጠሪያ አይደለም የሚሉትን ስሕተተኞች ካደረገ በኋላ ቀጠል አድርጎ (ገጽ 28-29 ላይ) "በገጠር ግን ክርስቲያን የሆነ አማራ እስላም ነህ ወይ ብሎ ቢጠየቅ የለም አማራ ነኝ ብሎ ሊመልስ ይችላል" ብሎ ራሱን በራሱ ያስተባብላል። የገጠሩ ሕዝብ ይኸንን ካለ ሌላ ማን ቀረ? ለነገሩማ እኔ እንደማውቀው ከሆነ መጻሕፍቱም እንደዚህ ነው የሚሉት።

የገጠር ነገር ከተነሣ፥ ደራሲው ለብሔረሰቦች በጋብቻ አለመደበላለቅ እንደትልቅ ማስረጃ አድርጎ የያዘው (ጋብቻ ሊፈጸም መቻሉንና በአጋጠመም ቍጥር በመፈጸም ላይ ያለ መሆኑን ወደጐን በመንፋት)፥ "አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ አርሶ አደሩ በሚኖርባቸው ገጠሮች ይህ ዓይነት ጋብቻ" አለመኖሩን ነው። "በአዲስ አበባና በአንዳንድ የደቡብ ከተሞች፥ በመሣፍንቱና በባላባቱ፥ በተለያዩ ብሄሮች ምሁራን መሃከል የሚታየውን ጋብቻ ብቻ ወስደን የሃገሪቱ ሁኔታ ዋንኛ መግለጫ ማድረግ ስህተት ነው" ይላል (ገጽ 16)። ቅድም ለገጠሩ ሁኔታ ዋጋ አልሰጠውም ነበረ፤ አሁን እንደትልቅ ማስረጃ አቀረበው። ለመሆኑስ አንድ የዳንግላ ገጠሬ ሕይወቱ ከሚያርሰው መሬት ጋራ ተሳስሮበት ሳለ፥ እንዴት አድርጎ ነው ከዳንግላ ተነሥቶ ከሐረር ቆንጆ ጋራ የሚጋባው? እንዲህ ያለውን ጋብቻ የሚከለክለው ብሔርተኝነት ነው ወይስ የአጋጣሚው አለመመቸት፤ ወይስ ሃይማኖት? "የአማራ ብሔረሰብ" በመሆናቸው የመንዝ (ሸዋ) ቆነጃጅትና የእነሴ (ጎጃም) ገበሬዎች በብዛት ሲጋቡ ምነው አላየን? እንደሰማሁትና እንዳነበብኩት፥ እኔ በምኖርበት ቀበሌ የሚኖሩ ገበሬዎች እንኳን ከሚኒሶታ ውጪ ሄደው ሊጋቡ ቀርቶ ከመንደራቸው እንኳን አንወጣም በማለት እርስ በርሳቸው ስለተጋቡ ልጆቻቸው በሽተኞች እየሆኑ ችግር ተፈጥሯል። ግን እንደማንኛውም የዚህ ሀገር ሰው እነሱም አሜሪካውያን ናቸው፤ ማንኛውም አሜሪካዊ (ካሊፎርኒያ ያለው ሳይቀር) ወገናቸው ነው።

**የአማራ ጥላቻ፤**

በደራሲው አስተያየት፥ "አማራነቴን ጠላሁ" የሚሉ ግለሰቦች ቁጥራቸው በርክቷል (ገጽ 19)። ይኸ ለኔ አዲስ ነገር ነው። ደራሲው እየደጋገመ፥ "እኛ አማሮች" በማለቱ ብቻ እሱን አማራ አድርጎ መቀበል እንዳይሆንብኝ (በዚያ ላይ ደግሞ እንደእሱ የሳይኪያትሪ ዕውቀት ያለኝ እንዳይመስልብኝ) ባልሰጋ አማራነቴን ጠላሁ የሚሉ ኢትዮጵያውያን ካሉ ከነሱ መካከል ዋነኛው ራሱ የዚች መጽሐፍ ደራሲ ነው እል ነበረ። ግን እሱን ትቼ ያለስጋት ይኸንን ማለት እችላለሁ፦

> ይቺን መጽሐፍ ሳነብ ልክ ኢጣልያኖች በሸዋ ላይ የጻፏቸውን መጻሕፍት የማነብ ነው የመሰለኝ።

ባሁኑ ጊዜ በአማሮች (በጠቅላላውም በኢትዮጵያ) ላይ ችግር የፈጠረው አማራነታቸውን የጠሉ ሰዎች ቊጥር “መበርከቱ” ሳይሆን አማራ ባለመሆናቸው የሚቆጩና የኢትዮጵያ ታሪክ የአማሮች ብቻ ታሪክ የሚመስላቸው ሰዎች ቊጥር መብዛቱ ይመስለኛል።

ይቺ መጽሐፍ የተዘጋጀችው በውስጥ-ዐዋቂ ሰው ስለሆነ እሷን ሳነብ ጊዜ በማጥፋቴ አልተቆጨሁም። ደራሲው ወያኔዎች ሊያጠፉዋቸው ያደፈጡባቸው እነማን እንደሆኑ በየገጹ ጠቁሟል። በገጽ 23-24 ላይማ ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው ቊጢጥ አርጎ አስቀምጧቸዋል፦

> ብሄሮች መብታቸውን ለማስከበር የሚያደርጉት ግፊት (የጎሳ ፖለቲካ ማለቱ ነው።) ከዚህ ቀደም እንደልቡ በሕዝቦች መብትና ሃብት ላይ ሲያዝ የነበረውን የተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል ማስቆጣቱ አልቀረም። (የጎሳ ፖለቲካን የምናወግዘውን ማለቱ ነው።) ይህ የሕብረተሰብ ክፍል በጥንቅሩ ከተለያዩ ብሄርና ብሄረሰቦች ገገር መደቦች የተውጣጣ ቢሆንም በዋንኛነት ከዘመናዊት ኢትዮጵያ ምስረታ ጀምሮ እስከአለንበት ዘመን ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ የበላይነቱን አስጠብቆ የኖረው የአማራው ገዥ መደብ ነው። ከዚህ ቀደም በመንግሥት የአስተዳደር መዋቅሮች በቢሮክራሲው፥ በጦር ሃይሉ፣ በፀጥታ፥ በፍርድ ሰጭነት በመንግሥታዊ የትምህርትና የምርምር ተቋማት፥ በውጭ ሃገሮች ዲፕሎማሲ ግንኙነት ሥራዎች ሥልጣን በመያዝ ከፍተኛ ተጠቃሚ የነበረው ይህ ሃይል ነው።

**የብሔር መታወቂያ ባንዲራ፣**

ደራሲው ተቃዋሚዎቹን አፍ ለማስያስዝ የሞከረው ገጽ 7-8 ላይ ባሰፈራቸው ከዚህ በታች ባሉት ቃላት ነው፦

> በኢትዮጵያ ውስጥ ከሰባ የሚበልጡ ብሄር ብሄረሰቦች መኖራቸውን ተቀብለው፥ ነገር ግን የብሄረተኝነትን ጥያቄ ሲመልሱ፥ በኢትዮጵያ የሚገኘው ብሄረተኝነት አንድ ኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነት ብቻ ነው የሚሉ አልታጡም። እንዲህ የሚሉ ሃይሎች ሊመልሱት የማይችሉት ጥያቄ አለ። ብሄረተኝነቱ ኢትዮጵያዊ ከሆነ ምን ዓይነት ቋንቋ ባህል፥ ታሪክ፥ ወግ፥ ወዘተ፥ በአጭሩ፥ ይዘቱ ምን ይሆናል የሚለውን ነው።

በደራሲው አስተሳሰብ የብሔር ማወቂያ (ባንዲራው) ቋንቋ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ቋንቋዎች ስላሉ ብሔረሰቦችም ቊጥራቸው በዚያው ልክ ሊሆን ነው--ከዚያም ላይበልጥ ከዚያም ላያንስ። በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ቋንቋ ብቻ ቢኖር ኖሮ ብሔርተኝነታችን ኢትዮጵያዊ ብቻ ይሆን ነበረ ሊል ነው። በብሔርተኝነት የሚጫረሱ ሱማሌዎች የሚናገሩት አንድ ቋንቋ እንደሆነ ደራሲው ያውቅ ይመስለኛል። ሰዉ ጎሳቸውን (ብሔራቸውን) አንድ ያደርግባቸዋል እንጂ እነሱን ቢጠይቋቸው ሱማሌነታቸውን ቢያምኑም ጎሳችን (ብሔራችን) አንድ ነው አይሉም። ተጠራቅማችሁ አንድ ብሔር፥ አንድ ሕዝብ፥ አንድ ሀገር፥ አንድ መንግሥት ሁኑ ብላ ያስቸገረቻቸው እንደ አቶ አንዳርጋቸው የምታስብ እንግሊዝ ናት። ዩጎዝላቢያ ውስጥ በብሔርተኝነት የሚተላለቁት ሰርቦች፥ ክሮዋቶች፥ ቦዝኒያውያን በቋንቋ አንድ ናቸው። ግን አንድ ጎሳ (አንድ ብሔር) ነን አላሉም። የብሔርተኝነት ምንጩ ቋንቋ ብቻ ቢሆን አየሪሾች ግማሾቹ ከእንግሊዝ ጋራ መሆንን ሲመርጡ ሌሎቹ መለየትን አይመርጡም ነበረ፣ አሜሪካና ካናዳ ሁለት ሀገር፥ ሁለት መንግሥት ባልሆኑም ነበር። ጌርማንያና ነምሳ ሁለት ሀገር፥ ሁለት መንግሥት ባልበሆኑም ነበር። የአሜሪካን ይሁዲዎች ቋንቋቸው እንደሌላው የአሜሪካ ሕዝብ እንግሊዝኛ ነው። የኦሮሞ ጎሳዎችን ጨፍልቆ አንድ ጎሳ (ወይም ብሔር) የሚያደርጋቸው ኃይል እስካልመጣ ድረስ ቋንቋቸው አንድ ስለሆነ ብቻ አንድ ጎሳ (ወይም ብሔር) ናቸው ማለት የሌለውን አለ ብሎ መናገር ነው። ጎንደሬውንና ጎጃሚውን የሚናገረው ቋንቋ አንድ ስለሆነ አንድ ጎሳ (ወይም ብሔረሰብ) ማድረግ ከነሱ የተለየ ቋንቋ የሚናገረውን ትግሬውን በቋንቋው ምክንያት ከጎንደሬው ይለያል ማለትን ያስከትላል። የእንግዲሁን አናውቀውም እንጂ እስከዛሬ እንዲህ አልነበረም።

**የብሔርተኝነት እዳ፣**

ደራሲው ለሐሳቡ መሠረት የጣለው ገጽ 12 ላይ ባሰፈራቸው

> በኢትዮጵያ ብሄሮች አሉ ብሄረተኝነትም ይኖራል። የብሄረተኝነት መፈጠር የራሱ መሠረት ስላለው ብቻ እንጂ በጉትጎታና በቅስቀሳ የመጣ አይደለም።

በሚሉት ቃላት ነው። እውነታቸው ግን በጉትጎታና በቅስቀሳ የመጣብን እዳ ነው። የደራሲውን አስተያየት የሚቀበል በኢትዮጵያ የብሔርተኝነትን ታሪክ የማያውቅ ሰው ነው። ታሪኩን የሚያውቅ (እንዲያውም ራሷን ይቺን ቁንጽል መጽሐፍ በጥሞና የሚያነባት) በኢትዮጵያ ብሔርተኝነት የተፈጠረው በሻዕቢያ አምላክነት እንደሆነ አይሰወረውም። አፈጣጠሩም÷ ብዙዎች ደጋግመው እንደጻፉትና እንደተናገሩት÷ "ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የሚቻለው የኢትዮጵያን ሕዝብ በብሔርተኝነት በማተራመስ ነው" በሚል ፍልስፍና ነው። ሻዕቢያ ሐሳቡን ያገኘው ከቅኝ ገዢዎች ነው። ቅኝ ገዢዎች ኢትዮጵያን ለመግዛት አለዚያም ለማዳከም የሚቻለው በሀገሪቱ ላይ የብሔርተኝነትን እሳት በማቀጣጠል ብቻ ነው ብለው በጊዜው ተጠቅመውበታል። ዛሬ ኤርትራ ራሷን የምትችል ሀገር ብትሆንልን በሀገራችን የጎሰኝነት ጉዳይ ገብ ይልልን ነበረ። ኤርትራ ራሷን እስካልቻለች (ግን የምትችል አይመስልም፤ ሐረግ ሬሳይቱ ያለዋርካው ድጋፍ ራሷን ችላ አልቆመችም፤) ወይም የኢትዮጵያ ሕዝብ በዴሞክራሲ እስካልተዳደረ ድረስ ሻዕቢያና ወያኔ ቅድሚያ የሚሰጡት ሀገሪቱን ለማዳበር ሳይሆን ጎሰኝነትን ለማፋፋም ነው።

ከሁሉ አስቀድመን መገንዘብ ያለብን ብሔርተኝነት ከውጪ የመጣ ሐሳብ እንጂ እኛ ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ የምንወግነው ለሀገራችንና ለሃይማኖታችን ነው። ብሔርተኝነት አለ ቢባል ሃይማኖታዊ÷ ግፋ ቢል ጎጣዊ ነው። ከአዲሲቱ ኢትዮጵያ ይጠበቅ የነበረው ሃይማኖትን የግል አድርገን ውገናችንን በሀገር ላይ ብቻ ማድረግን ነበረ። በዚህ ረገድ የተደረገው ጥረት ብዙ ባይገፋበትም የተገፋውን ያህል ውጤት ማሳየት ጀምሮ ነበረ። አሁን ግን "ጎሳ የጋራ÷ ሃይማኖት የሚያጣላ÷ ሀገር የግል" የሚል ፈሊጥ ሊያመጡብን ነው። እስከዛሬ ለብሔር ብሔረሰብ ፖለቲካዊ ዋጋ እንዳልሰጠነው ሶስት ማስረጃዎች አሉ፦

አንደኛ÷ ብሔር/ብሔረሰብ የሚባለው ቃል በዛሬ ትርጉሙ በቋንቋችንም አልነበረም። የተፈጠረው አሁን በኛ ዘመን ነው። የፈጠሩትም ብሔርተኝነትን ያመጡብን የኢትዮጵያ አንድነት ጠላቶች ናቸው። እዚሁ ሀገራችን ውስጥ የበቀለ ቢሆን ኖሮ ሀገራችን ውስጥ እንደበቀለው እንደ ማንኛውም ነገር ሁሉ ስም ይዞ እናገኘው ነበረ። ደራሲው "ብሄር ሲባል ከቀጥታ ትርጉሙም ከስሜቱም ተነስተን በምዕራፍ 1 ከቀረበው ሀተታ ጋር አገናዝበን ስናየው ኦሮሞ÷ ትግሬ÷ አፋር ቢል ትክክልም ተገቢም ይመስላል" ይላል። ተሳስቷል፤ ትክክልም ተገቢም አይመስልም፤ አይደለምም። "ብሔር" የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙ "ሀገር" ማለት ነው። ቃሉ ምድርን እንጂ ሕዝብን አያመለክትም። እንዲህ ከሆነ አንድ ኢትዮጵያዊ ብሔሩን ሲጠይቁት ኢትዮጵያ÷ ቡልጋ÷ ጎንደር÷ ኢሉባቦር÷ መንደፈራ ቢል ምኑ ነው "ግር የሚያሰኘው" (ገጽ 14)?

ወደድነውም ጠላነውም ለዚህ ሐሳብ እንጠቀምባቸው የነበሩ ቃላት÷ "ዘር"÷ "ነገድ"÷ "ጎሳ"÷ "ቤት"÷ "ወረ" (ለምሳሌ÷ ወረ ቃሉ÷ ወረ ኢሉ÷ ወዘተ) ናቸው። "ዘር" ጠባብና ሰፊ ትርጉም ነበረው (በገጠር ውስጥ ዛሬም አለው)። በጠባብ ትርጉሙ ባል በሚስቱ ማሕፀን የሚዘራው ዘር ነው። ያ ዘር ሰው ሆኖ ሲወለድ "የእገሌ ልጅ"÷ "የእገሌ ዘር" ይባላል። ለምሳሌ÷ ከበደና በቀለ ያንድ ሰው ዘር (ወንድማማቾች) ናቸው እንበል። የነሱ ልጆች ደግሞ በአያታቸው ያንድ ሰው ዘር (scion) ሲባሉ÷ በአባታቸው የሁለት ሰዎች ዘሮች ናቸው፤ የከበደ ልጅ የበቀለ ዘር÷ የበቀለ ልጅ የከበደ ዘር አይደሉም። በአያት ያንድ ሰው ዘር ናቸው፤ በአባት ግን አይደሉም።

"ዘር" በሰፊው ትርጉሙ (ልክ ባይሆንም) በልማድ ቋንቋን ያመለክታል። አማርኛ የሚናገረውን የአማራ ዘር ይሉታል፤ ኦሮምኛ የሚናገረውን የኦሮሞ ዘር ይሉታል፤ ጥንት ሳይደበላለቁ በአባት የአንድ ሰው ዘር ሳይሆኑ አይቀሩም ከማለት የመጣ ነው። ይኸም ሆኖ "ዘረኛ" "ዘረኝነት" ማለት የመጣው "racist, racism" የሚሉትን የውጭ ቃላት መተርጎም ስላለብን ነው።

ሁለተኛ፥ ለብሔረሰብ ማኅበራዊ ዋጋ አንሰጠውም። ከሁለት ብሔረሰብ የሚመጡ ሰዎች ያለብዙ ተቃውሞ የሚጋቡ ከሆነ የብሔረሰቡ ብሔረሰብነት አፍአዊ ወይም ሌላ ነገር ነው። አማሮችና ትግሬዎች ይጋባሉ ወይስ አይጋቡም? አማሮችና ኦሮሞዎች ይጋባሉ ወይስ አይጋቡም? አኙዋኮችና አማሮች ይጋባሉ ወይስ አይጋቡም? እስላሞችና ክርስቲያኖች ይጋባሉ ወይስ አይጋቡም? እስራኤላውያንና ዐረቦች ይጋባሉ ወይስ አይጋቡም? ፈላሻዎች (አይሁዶች) እና ክርስቲያኖች ይጋባሉ ወይስ አይጋቡም? በህንድ ሀገር ሂንዱዎችና እስላሞች ይጋባሉ ወይስ አይጋቡም? በቆጵሮስ ግሪኮችና ቱርኮች ይጋባሉ ወይስ አይጋቡም? አብረው ይበላሉ ወይስ አይበሉም? የብሔርን ድምበር በጋብቻ የማይተላለፉ ዘሮች (ወይም ብሔረሰቦች) እንደሚተላለፉቱ አይደሉም።

ሦስተኛ፥ ለብሔረሰበ (ለጎሳ) ፖለቲካዊ ዋጋ አንሰጠውም። አንድ ሰው ትግሬ በመሆኑ ምክንያት ከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን ከመያዝ ይከለከላል ወይስ አይከለከልም? አንድ ኦሮሞ፥ ጉራጌ፥ ሐዲያ፥ አማራ፥ ወዘተ በጎሳው ምክንያት ለሱ የፖለቲካው ዓለም ዝግ ነው ወይስ አይደለም? ጳጳስ፥ ሼኽ፥ ኢማም፥ ሊቀ ጳጳስ መሆን ይችላል ወይስ አይችልም?

በሀገራችን (በታሪካችን ሳይቀር) ልዩነት አለ ቢባል የሃይማኖትና የመልክ ነው። እሱውም ቢሆን ከሌላው ሀገር ጋራ ሲተያይ በሕዝብ ደረጃ በሚያስደንቅ ሁኔታ በመቻቻል በሰላም አብረን ኖረናል። በኛ ዘመን ደግሞ ትምህርት እየገፋ፥ ዕውቀት እየተስፋፋ ሲሄድ አንዱ የሌላውን ሃይማኖት መናቁን ትቷል።

## አዳዲስ የታሪክ መምህራን፤

ደራሲው እነዚህ ጋብቻና ዕውቀት የሚሏቸው ነገሮች በኢትዮጵያ ውስጥ የወያኔ የብሔርተኝነት ፖለቲካ እንዳይስፋፋ የሚያደናቅፉ ደንቃራዎች መሆናቸውን በማፌዝና በምሬት ጽፉዋል። መገረም የለብንም፤ "እገሌ እኮ ምሁር ነው፤ የዩኒበርስቲ ዲግሪ አለው" ብሎ በሰዎች ምሁርነት ከት ብሎ መሣቅ በኮሚኒስቶች ዘንድ የተለመደ ነገር ነው። "ከሁለት ብሄር" የተወለዱትንማ መታከም የሚያስፈልጋቸው በሽተኞች ማለት ነው የቀረው።

በደራሲው አስተያየት "ከሁለት ብሄር መወለድ" ችግር ቢፈጥርም በከተማው እንጂ በገጠሩ ሁሉም በክልሉ ተከልሎ በንጽሕና ነው የሚኖረው። ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ፥ ሰፊው የአማራ ሕዝብ፥ ሰፊው የጉራጌ ሕዝብ፥ ወዘተ ሌላ ዘር የለበትም ባይ ነው። ታሪክ የሚለው ግን ሌላ ነው።

ዛሬ ፊደል የቈጠረና ሌላ ትምህርት (ሕግ፥ ንግድ፥ ወዘተ) የተማረ ሁሉ የኢትዮጵያን ታሪክ ጸሐፊና ተንታኝ በሆነበት ዘመን ታሪክ ከላሾች ሊያስተምሩን የሚፈልጉት በኢትዮጵያ ውስጥ ይደረጉ የነበሩ የእርስ በርስ ጦርነቶች የብሔረሰቦች ጦርነቶች መሆናቸውን ነው። እነሱን ትተን በያዝናት መጽሐፍት እንወሰንና፥ ደራሲዋ ይኸንኑ እምነት ይዞ ሲገሠግሥ አላስኬድ የሚለውን እንደሌላ ይቆጥረዋል፦

> ኢትዮጵያ ዛሬ በውስጧ የያዘቻቸውን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦች ያቀፈች
> አንድ ሀገር ለማድረግ የመደመሪያው እርምጃ ከተወሰደበት ዕለት ጀምሮ የሃገራችን
> ፖለቲካ ብሔራዊ ይዘት ነበረው ብንል አንሳሳትም

ይላል (ገጽ 33)። "ብሔራዊ ይዘት" ማለቱ የጎሳ ፖለቲካ፥ አንዱን ጎሳ ሌላው ጎሳ የሚያጠቃበት ዘመን ማለቱ ነው። ይኸንንም ግልጽ ሲያደርግልን "አጼ ምኒልክ አማርኛ ተናጋሪ ያልሆነውን የሰሜን ሆነ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ ያስገበሩት በሸዋ መሳፍንትና መኳንንት በሚመራው የሸዋ አማራ ሠራዊት ነበር" ይላል። አማራ ያልነበሩት እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፥ እነደጃች ባልቻ፥ እነራስ ጎበና ዳጨ ከቍጥር አይገቡም(!)። ሸዋ የብዙ ጎሳዎች አውራጃ መሆኗ እየታወቀ ሠራዊቱ (የነራስ ጎበና ሠራዊት ሳይቀር) አማራ ብቻ ነበረ የሚለን በይሆናል እንጂ በማስረጃ አይደለም።

ወያኔዎች ከትግራይ ስለሆኑ ዛሬ ኢትዮጵያን አፍኖ የያዘው ወታደር የትግራይ ሠራዊት ብቻ ነው ሊለን ነው።

ይኸን እነተወው፤ ግን አፄ ምኒልክ የአማራውን ሀገርስ አላስገበሩም ነበር ወይ? እንዴት ነው ይኸስ "ብሔራዊ" (ጎሳዊ) የሚሆነው ሲሉት ደራሲው በተለመደው የአጻጻፍ ስልቱ ተሽቀዳድሞ "ይህ ማለት የየራሳቸው ንጉሶች የነበራቸው አማርኛ ተናጋሪ የሆኑ ክልሎችን አጼ ምኒልክ በወታደራዊ ኃይል አላስገበሩም ማለት አይደለም" በማለት የራሱን አዎንታ በራሱ አሉታ ይደመስሰዋል። ታዲያ ይኸ ከሌላው በምን ይለያል፥ ምን ማለት ነው፥ ሲሉት የሚቀጥለውን መልስ ይሰጣል፦

> የወሎና የጐጃም ንጉሶችን መገበርን ልዩ(!) የሚያደርገው ነገር ግን አለ። በእነዚህ ክልሎች የሚነሱ ንጉሶች የአማራውን ሕዝብ በበላይነት ለማስተዳደር አማራነታቸውን መሠረት የሚያደርጉ ነበሩና በመሃከላቸው ትግሉ ብሔራዊ (=ጎሳዊ) ልዩነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፥ ክልላዊ መሆኑ ነው። ሌሎች ሕዝቦችን የማስገበር ሂደቱ ግን በግልፅ ብሔራዊ (=ጎሳዊ) ይዘት እንደነበረው ማየት ይቻላል።

አንድን አውራጃ ማስገበር ሌላውን አውራጃ ከማስገበር የሚለይበትን ነገር ማየት እንዴት ነው የሚቻለው? የኢትዮጵያ ነገሥታት በየትኛውም አውራጃ ሲዘምቱ ዓላማቸው አንድ ነበረ፤ ይኸም ሰፊ ኢትዮጵያን መግዛት ነው። የሚያስገብሩት ሕዝብ አማርኛ ቢናገር፤ ኦሮምኛ ቢናገር፤ ጉራጌኛ ቢናገር፤ ትግርኛ ቢናገር፤ ሱማልኛ ቢናገር፤ እስላም ቢሆን ወይንም ክርስቲያን ለነሱ ምንም ልዩነት አያመጣም ነበረ። ዛሬ ወያኔዎች ለግል ጉዳያቸው አንዱ ነገድ ሌላውን በድሏል እያሉ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ጎሳዊ መንግሥታት ለማቋቋም በቀጥታና በእጅ አዙር ቢጥሩም፥ "አዎን፥ አዎን" የሚላቸው አጫፋሪ ቢበዛዘም፥ ነገሥታቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እኩል ነበር የዘመቱበትና ያስገበሩት።

ደራዊው "አጼ ቴዎድሮስ ወደንጉሠ ነገሥትነት ሲያመሩ ተቀናቃኞቻቸውን የጐንደር መሣፍንቶች መነን(ን)ና ልጅዋን እራስ ዓሊን የተዋጉበት ዋንኛው የፖለቲካ መሣሪያ የራሳቸውን አማራነትና የእነሱን የየጁ ኦሮሞነት በማስረገጥ ስለነበር ለአማራው ብሔርተኝነት ማበብ በአመለካከት ደረጃ በአማራው ሕዝብ ውስጥ ለም መሬት ፈጥረው ነበረ" ይለናል። ዛሬ ወያኔዎች እንደሚያደርጉት በዘር የመጡብን መስሎታል። አንደኛ፥ አፄ ቴዎድሮስ ከእቴጌ መነን ጋራ ጋብቻ ነበሩ። ሁለተኛ፥ ንጉሡ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር የመለየት ሐሳብ አልነበረባቸውም። እንደቀድሞው ሥርዓት የሀገሪቱ መንግሥት የክርስቲያን መንግሥት ስለነበረ "አማራና ጋላ" ሲያነጻጽሩ "ክርስቲያንና እስላም" ማለታቸው እንጂ የአማራውን ዘር ለማልማት የዳበረ መሬት ለመፍጠር አልነበረም።

ደራሲው ታሪካችንን ሲተነትን " . . . የሃገሪቷ ምስረታ በአንድ ብሔር መሳፍንት በዋነኛነት ያውም በአንድ ክልል በሚገኝ የሸዋ አማራ መሳፍንት የሃይል እርምጃ የተከናወነ ነበር ማለት ይቻላል" ይላል። ይኸ አነጋገር ካለማወቅ የመነጨ ነው ወይስ ታሪክን ዐውቆ ለማቆላመም ተፈልጎ ነው።

የአቀራረቡን ስሕተትነት በምሳሌ ላሳይ እፈልጋለሁ። አንድ ከሰሜን ተነሥቶ ወደደቡብ የሚወርድ ወንዝ አለ እንበል። ውሀው ጠበልነት አለው፤ በሱ የተጠመቀ ሁሉ ከብዙ ዓይነት በሽታ ይፈወሳል። ችግሩ ወንዙ ገደል ለገደል ስለሚወርድ በሽተኞች ሊደርሱበት የሚችሉት በአንዳንድ በተወሰኑ ቦታዎች (መልካዎች) ላይ ብቻ ነው። እንግዲህ በሽተኞቹ በነዚያ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ውሀውን ደርሰውበት ሲፈወሱ፥ ፈወሰን የሚሉት ማንን ነው። የወንዙን ውሀ (ጠበሉን) ነው ወይስ በተለየ የዚያን ቦታ ውሀ? ወንዙ የኢትዮጵያ መንግሥት ረጅም ታሪክ ነው። ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የዚያ መንግሥት ፍልስፍና ሰፊይቱን ኢትዮጵያ ማቆየት (ጠበልነት) ነበረ። ሥልጣኑን በዋነኝነት የሚይዙ ጉልበተኛ መሪዎች ሁሉ ፍልስፍናውን ተከትለው እነሱን ለሚተካ ትውልድ ሰፊ ኢትዮጵያን (በነሱ እምነት የተፈወሰች ኢትዮጵያን) ለማስተላለፍ ሞክረዋል። የቀናቸውም (ያሰፉዋት) ያልቀናቸውም (ያላሰፉዋት) አሉ። እንደወንዙ ውሀ (ጠበል) ነው፤ የሚደረስበትም የማይደረስበትም ቦታ አለ ብለናል። ከቀናቸው ነገሥታት ማህል (ለበሽተኞች

አመች ከሆኑት ስፍራዎች ማህል እንደ ማለት ነው) አንዱ አፄ ምኒልክና ሸዋ ነበሩ። ሰፊዋን ኢትዮጵያን ገዝተው ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ ከሌሎቹ ይልቅ እኚህን የሸዋውን አፄ ምኒልክን ቀናቸው እንጂ እሳቸው ፍልስፍናውን በማክበር ረገድ "በዋነኛነት" ኢትዮጵያን ከመሩት ከሌሎቹ ነገሥታት በምንም አይለዩም፤ ሌሎቹም ከሳቸው በምንም አይለዩም። የምኒልክ ሸዋም ከቴዎድሮስ ጎንደር ወይም ከዮሐንስ ትግራይ ይበልጥ ወይም ያነሰ ወይም በተለየ ሁኔታ የምትወቀስበት ወይም የምትታማበት ምክንያት የለም። የአፄ ምኒልክ "ሲንድሮም" እንደያዘው ከሳቸው አንላቀቅም ከማለት ይልቅ ወደ ኋላቸውም ወደፊታቸውም ብንሄድ እንደሳቸው የቀናቸው ገዢዎች እናገኛለን። ወደኋላ ስንሄድ ድግና ዣንን፥ ዓምደ ጽዮንን፥ ግራኝ መሐመድን (አሕመድ ኢብራሂምን) እናገኛለን። ወደፊት ስንሄድ ኢጣልያን፥ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ።

እነዚህ እያንዳንዳቸው ኢትዮጵያን አስፋፍተው አልፈዋል። በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ውስጥ ሀገሪቱ ተከፋፈለች የሚባልበት ዘመነ መሳፍንት እንደ "ትናንት" የሚታይና በቅጽበት እንዳለፈ የሚቆጠር ዘመን ነው። የኦሮሞዎች ወረራም "የትናንት ወዲያ" ታሪክ ነው። ኢትዮጵያ ከነዚህ "ከትናንትናዎች" እና "ከትናንትና ወዲያዎች" በፊት ከዛሬው ስፋቷ ይበልጥ ሆና ብዙ ዘመናት ኖራለች። አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ሲነሡ፥ አፄ ዮሐንስ ያንኑ ሲገፉበት፥ አፄ ምኒልክ በዚያው ሲቀጥሉበት፥ አፄ ኃይለ ሥላሴ የሀገሪቱን ድምበር ከባሕር ጠረፍ ሲያደርሱ አዲስ ፍልስፍና አምጥተው፥ ቀድሞ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ መሬት ለመያዝ አስበው አይደለም፤ አልያዙምም። እንኳን ሊይዙ ሁሉንም አላስመለሱም። አፄ ምኒልክ የኢትዮጵያን ዳር ድምበር የቻሉትን ያህል ለማስመለስ ከሌሎቹ ነገሥታት ይበልጥ የቀናቸው ከሌሎቹ የተሻለ ዕድል አግኝተው ወይም ሌላ ፍልስፍና አምጥተው ሳይሆን ከሌሎቹ የበለጠ ብልህ በመሆናቸውና የዘመናቸውን ፖለቲካ በግልጽ ለማየት በመቻላቸው ብቻ ነው።

**የጎሰኝነት ትርጉም፤**

የጎሰኝነት (የብሔርተኝነት) ትርጕም ለደራሲው እንደመሰለው ቀላል ነገር አይደለም። ስለዚህ ጉዳይ የጻፉት እነ እስታሊን ብቻ አይደሉም፤ ብዙ ታላላቅ የምዕራብ ሊቃውንት የጻፉትን ማንበብ አይጎዳም። ደራሲው አንድ ሰው "እኔ ኦሮሞ ነኝ፤ አማራ ነኝ፤ ጉራጌ ነኝ፤ ወላይታ ነኝ፤ ወዘተ" ካለ በውስጡ የተኛ ብሔርተኝነት አለና እሱ ተቀስቅሶ መኰትኰት መዳበር አለበት ባይ ነው። እርግጥ ብሔርተኝነት ሊቀሰቀስ የሚችል የተኛ ኃይል ነው፤ ተሞክሮ ሲሠራም አይተናል። ግን እዚህ ላይ ብዙ የሚነሡ ነጥቦች አሉ፦

አንደኛ፥ አንድ ሰው ለምሳሌ "እኔ አማራ ነኝ" ሲል ምን ለማለት እንደሚፈልግ ከራሱ ከተናጋሪው በቀር በትክክል የሚያውቅ የለም። የሚነግረን የራሱን ምንነት ነው ወይስ ወገኖቹ እነማን እንደሆኑ ነው? አማራ ነን የማይሉትን ኢትዮጵያውያን አማራ ነን ባለማለታቸው ብቻ ወገኖቹ ካላደረጋቸው (ከነዲንቃ፥ ከነሀጎስ፥ ወዘተ ጋራ ወዳጅ አባል መሆን ካልፈለገ) የሚነግረን ስለምንነቱ ሳይሆን ስለወገኖቹ (ከማን ጋራ እንደሚወግን፥ ከማን ጋራ እንደሚውል እንደሚያድር፥ ከማን ጋራ የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋም እንደሚፈልግ) ነው፤ የአማራው ወገን ነኝ ማለቱ ነው። ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወገኔ ነው ካለ (ከማንም ኢትዮጵያዊ ጋራ ከወገነ፥ ከማንም ኢትዮጵያዊ ጋራ ከዋለ ካደረ፥ ከማንም ኢትዮጵያዊ ጋራ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ከሆነ) በዚያ ባነጋገሩ ሊገልጽልን የፈለገው ስለራሱ ምንነት ነው እንጂ ስለወገኖቹ አይደለም።

ስለራሱ ምንነት ብዙ ሌላ ነገር ሊነግረን ይችላል። እኔ አማራ ነኝ እንዳለው እኔ ቡልጌ ነኝ፥ እኔ ቀይ ነኝ፥ እኔ አጭር ነኝ፥ እኔ፥ ቀጪን ነኝ፥ እኔ ወንድ ነኝ፥ እኔ በራ ነኝ፥ እኔ ሐኪም ነኝ፥ ወዘተ ሊለን ይችላል። እነዚህ ሁሉ የሰውየውን ማንነት መግለጫ ቃላት ናቸው። ጥቅም አላቸው፤ ለምሳሌ፥ አንድ ጥቍር ወይም ረጅም ወይም ወፍራም ሰው በወንጀል ቢፈለግ ይኸ ሰው በጥርጣሬ እያዝ ይሆናል ብሎ ምንም አይሰጋም። ልብስ ለመግዛት ቢፈልግ ደግሞ የወንድ ልብስ ተራ ይሄዳል፥ አጭሮችና ቀጭኖች የሚመርጡትን ይመርጣል። ሲነጋገርም እንደልቡ ለማውራት ቋንቋቸው ወደሚገባቸው ሰዎች ጠጋ ይላል። አማራ ሆኖ ጉራግኛ መናገር ከቻለም ወይም ጉራጌዎቹ አማርኛ መናገር ከቻሉ ሌላ ምክንያት ከሌለው (ለምሳሌ፥ አብሮ አደጎቹን ከሌላ ዘንድ ካላየ) እነሱ አጠገቡ

እያሉ አማራ ነኝ የሚል ሰው ፍለጋ አይሄድም። ባጭሩ የሸዋ አማራ ወገን ሲፈልግ አጠገቡ ያሉትን ጉራጌዎች አልፎ ጎጃሜ ፍለጋ አይሄድም።

ሁለተኛ፥ ብሔርን ማወቅ (አማራ ነኝ፥ ጉራጌ ነኝ፥ ወዘተ ማለት) ብሔርተኝነት አይደለም። ቁመትን ማወቅ ቁመተኝነት አይደለም። ቁመተኝነት "እኛ አጭሮች" ማለት ሲመጣ ነው። አጭር የሆንክ ሁሉ ተነሣ፤ መሣሪያህን አንሣ ሲሉት ካነሣ ነው። ይኸም የሚሆነው ከሁለት መንገድ ባንድ ነው፡- (1) አንድ ተንኮለኛ ሰው ተነሥቶ አንድ ረጅም መሪ በሰው ሁሉ ላይ ያደረሰውን በደል ባጭሮች ላይ ብቻ ያደረሰ አድርጎ አሰማምሮ፥ ላጭሮች አቅርቦ አጭሮች ሲታለሉለት፥ ወይም (2) እውነትም አጭር አጭሩ እየተለቀመ ከነሕይወቱ ገደል ሲወረወር፥ በቤት ውስጥ ታጉሮ በእሳት ሲቃጠል፥ በቢላዎ ሲታረድ አጭር አጭሩ ራሱን ለመከላከል ሲጠራራ ነው። እንዲሁ ብሔርተኝነትም ድንገት አይጀመርም፤ የሚጀመረው ለምሳሌ (1) አቶ አንዳርጋቸው ኢትዮጵያን በጎሳ ለመከፋፈል በሚደረገው ጥረት ድርሻውን ለማበርከት እንደሚያደርገው፥ "የሸዋ አማሮች እኛን አማሮችን በድለውናል" ሲል ተቀባይ ያገኘ እንደሆነ፥ ወይም (2) በወያኔዎች አበረታችነት በተለየ በአማራውና በክርስቲያኑ ሕዝብ ላይ እውነተኛ ጥቃት ሲደርስ ለመከላከል እንደ መአሕድ በዘር ለመደራጀት መገደድ ሊመጣ ነው።

በኢትዮጵያ የጎሳ ንቅናቄ ምክንያቶች እነዚህ ሁለቱ ናቸው። ሥልጣን የጠማቸው ጥቂት ሰዎች የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ የበለጠ እንደተበደለ ነገሩት፤ በዚህም ምክንያት ከጎንደር ሕዝብ ልዩነት ከሌለው ከትግራይ ሕዝብ የተወለደው ወጣት እውነት መሰለው። ከሸዋ አማራ ልዩነት የሌለው የሸዋ ኦሮሞ የሸዋ አማራ ይበድልሃል እየተባለ በወያኔዎችና በጥገኞቻቸው ቀን ተሌት ይነገረዋል።

"የመጽሐፉችን" ደራሲ የአማራው ሕዝብ እንዴት በሸዋ አማሮች እንደተጠቃ ይናገራል። ወያኔዎች ሲቀናቸው ስላየ እነሱ በትግራይ ወጣት ላይ ያፈሰሱትን የማስቆጫ ቃላት የጐጃም፥ የጐንደር፥ የወሎ፥ የሰሜን ሸዋ ሕዝብ እንዲሰማው በመጽሐፉ የመጨረሻዎቹ አራት ገጾች ላይ አፍስሷል። ይኸንን ያደረገው አማርኛ ተናጋሪው ሕዝብ በብሔርተኝነት አንድነትና ጥቃት ተሰምቶት ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ራሱን ለይቶ በክልል እንዲወሰን (ነፃ እንዲወጣ) ነው እንጂ ለጥቃቱ ተቆርቁሮ አይደለም። መአሕድን በእሱ መምሪያ እንዲሄድ ጠራው እንጂ ድርጅቱ ለአማራው ሕዝብ መብት፥ ለኢትዮጵያ አንድነት ስለሚያደርገው ትግል አንዲት ቃል አይናገርም። ኢትዮጵያ በክልል ስትከተፍ የአማርኛ ተናጋሪው ሕዝብ መስፈሪያ ነው ከተባለው እንኳን ከሰሜን ወሎና ከሰሜን ጎንደር ከሸዋም ላይ ተቈርሶ ሌሎች ናቸው ለተባሉ ጎሳዎች መሰጠቱ አልቆረቆረውም። ለምን እንደሆነ የወሎ፥ የጎንደር፥ የሸዋ ሕዝብ አያውቅም ብሎ እንደሆነ የነዚያ አውራጃዎችን ሰው መናቅ ነው።

ሦስተኛ፥ ብሔረሰብነት ሰዎች የሚለውጡት ነው። እርግጥ እንደልብስ በአንድ ቀን ወይም በአንድ ትውልድ የሚቀየር አይደለም። ግን በረጅሙ የታሪክ ዘመን አንድ ሕዝብ ካንድ ብሔረሰብነት ወደሌላ ብሔረሰብ የሚለወጥ መሆኑን የማንም ሀገር ታሪክና የሊቃውንቱ ጥናት ይመሰክራሉ። በኮሚኒስት ቻይና ከሁለት ብሔረሰብ የተወለደ ልጅ ለአቅመ አዳም ሲደርስ ከሁለቱ አንዱን መርጦ ወደ አንዱ ይጠቃለላል። ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን ከትግራይነትና ከኦሮሞነት አንዱን መርጦ እንደመያዝ ማለት ነው። ይኸም ዛሬ አንድ ብሔረሰብ ካልወጣህ እየተባለ የሚጨቀጨቀው አማርኛ ተናጋሪው ሕዝብ በዓሥር ከሚቆጠሩ ጎሳዎች (ከብዙ ዓይነት አገሮች፥ ከብዙ ዓይነት ጋፋቶች፥ ወዘተ) የተውጣጣ ነው። እንዲያውም እናት የአንድ ጎሳ (ትግራይ፥ ወዘተ) አባት የሌላ ጎሳ (ኦሮሞ፥ ወዘተ) የሆኑ ሰዎች የወለዷቸው ብዙ "አማራዎች" እናውቃለን። ወደፊትም ቢሆን ብሔረሰቦች በዚያው በታጐሩበት ዘብጥያ ካልተቆመባቸው በዚያው በያዙት ብሔረሰብነት ጸንተው የሚኖሩ አይደሉም፤ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው እንደተለወጡት የእነሱም ዘሮች ይለወጣሉ።

አራተኛ፥ ጎሳዎች የሚከፋፈሉት በቋንቋ ብቻ አይደለም፥ የራሳቸው የሆነ ታሪካዊ አከፋፈል አላቸው። ለዚህም ምሳሌ የሚሆኑት ኦሮሞዎች፥ ሱማሌዎች እና ጉራጌዎች ናቸው። እነዚህ ሦስት ጎሳዎች አይደሉም፤ በጣም ብዙዎች ናቸው። እንጠይቃቸውና ይናገሩ፤ የሚሉትንም እንመን።

ከባለቤት ያወቀ ቡዳ ነው። እና፥ ሁሉም በየጎሳቸው ይደራጁ ወይስ አይደራጁ? አንድ ሰው "ኢትዮጵያውያን በሀገራዊነት (በኢትዮጵያዊነት) ከመደራጀታቸው በፊት በብሔር መደራጀት ያስፈልጋቸዋል" ባለበት አፉ እንዴት አድርጎ እነዚህን የቍጥር ንኡሳን ጎሳዎች ተለያይታችሁ አትደራጁ ለማለት ይችላል? ይኸማ በአንድ ራስ ሁለት መላስ ሊሆን ነው!

አምስተኛ፥ የጎሰኝነት መሠረቱ እግዜር-ሠራሽ (ውልደት -primordial) ቢሆንም፣ መዋቅሩ ሀገር ለመገንባት ሰው-ሠራሽ፥ ሀገር ለመከፋፈል ሰይጣን-ሠራሽ፥ (instrumental) ነው። ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆን የአዘርባይገን ሪፑብሊክ በቀደሞ የሶቪየት ኅብረት ፖለቲከኞች አፈጣጠር ነው--እምነበ አልቦ። ባጭሩ፥ ጎሰኝነትና ሀገራዊነት (በኛ ሀገር ኢትዮጵያዊነት) ሁለቱም እኩል ሊቀሰቀሱ የሚችሉ ስሜቶች ናቸው። ሆኖም የጎሰኝነት ስሜታችን የተቀሰቀሰ እንደሆነ በጎሳ ይከፋፍለናል፣ የሀገራዊነት ስሜታችን የተቀሰቀሰ እንደሆነ ግን አንድ ያደርገናል፣ እንደጥንቱ እንጋባለን፣ እንደዛሬው ባንድ የፖለቲካ ፓርቲ እንሰለፋለን።

ታዲያ ምነው አቶ አንዳርጋቸው አቶ ከፋፍላቸውን ሆነብን? ለምንድነው አንድ የሚያደርገንን ትቶ የሚከፋፍለንን የመረጠው? ብሔርተኝነት (ጎሰኝነት) ሀገርን ከመከፋፈል በቀር ሌላ ምን ጥቅም አለው? ጎሰኝነትን ሀገር ከፋፋዮች ይፈልጉት እንጂ ለሀገር ወዳጁ ምን ያደርግለታል። አርባ አምስት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ባንድነት መሰለፍ ከቻሉ የዓሥራ አራቱ "ክልል" ኢትዮጵያውያን በአንድ ኢትዮጵያዊነት እንዳይዋሐዱ የሚከለከሉት ለምንድን ነው? አድልዎ እንዲቀር ነው? መንዜዎች ለአማራው ብሔር እንጂ ለመንዜዎች፣ አድዋዎች ለትግራይ ብሔር እንጂ ለአድዋዎች ማዳላታቸው እንዲቀር ነው? ይኸንን መጥፎ ሰብአዊ ጠባይ ለማስተው ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ብሔርተኝነት ይሻላል? አንድ ኢትዮጵያዊ በቋንቋው እየተለየ "አንተ ከዚህ አትለፍ" ከተባለ ወይም ቋንቋቸውን ከማያውቀው ዘመዶቹ ማህል ሲገኝ ቋንቋውንና ቋንቋቸውን አስተምሮ ከማቀራረብ ይልቅ እንደ ሌላ ሕዝብ እንዲታይ ከተደረገ በኋላ እንዴት የአንድ ሀገር ሕዝብ ሊሆን ይችላል? ምነው ይኸ መጥፎ ጠባይ ስዊዘርላንድ ውስጥ የለም? ሩቅ ሳንሄድ፥ ምነው ኤርትራ ውስጥ ክልል ክልክል ነው?

ኢትዮጵያዊነትን ከጎሰኝነት በላይ ለምን ማየት እንደማይቻል ደራሲው የሚያስገርም መልስ አለው:-

> *አማራነታችንን ትተን ኢትዮጵያዊያን ነን እንዳንል ኢትዮጵያዊነት የኛ ብቻ ሳይሆን እኛንና የሌሎቹን ብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦችን ጨምሮ የወል መጠሪያችን ነው የሚል ጽኑ እምነት ስላለን ለብቻችን ልንጠቀምበት የምንችል ቃል አልሆነም። . . . ጐንደሬ፥ ጐጃሜ፥ ወሎዬ፥ ምንጃሬ፥ ቡልጌ፥ መንዜ፥ ወዘተ. እያልን እንዳንሄድ . . . እኔ ማነኝ የሚል ጥያቄ የምናነሳው ሁላችንም በጋራ ሆኗል።*

የደራሲው አስተሳሰብ "ኢትዮጵያዊነትን የማንፈልገው የጋራ ስም ስለሆነ ነው፣ አማራነትን የምንፈልገው ግን የጋራ ስም ስለሆነ ነው" የሚል ነው፣ የሰውየው ጨዋታ ትዝ አለኝ:- ሰውየው አንድ ወጣት ከደብረ ታቦር ወደ ጎንደር ሲገሠግሥ አይቶ፥ "ወጣት ወዴት ነው እየተጣደፍክ የምትሄደው?" ብሎ ጠየቀው። "ወደ ጎንደር" ብሎ ቢመልስለት፥ "እንደዚያስ ከሆነ ተወው፣ ሂድ አላቁምህ፣ እኔ ደሞ ወደ ጎንደር የምትሄድ መስሎኝ መልክት እንድታደርስልኝ ልለምንህ ነበረ" አለው ይባላል።

የግል እምነት

በእኔ እምነት በኢትዮጵያ ውስጥ በዘር መደራጀት ተጐንጉኖ ልብስ የሆነውን ልዩ ልዩ መልክ ያለውን አሮጌ የሱፍ ክር እንደመተርተር፥ አልተረተርም ካለ እንደመበጣጠስ፥ እንደመቦጫጨቅ የሚቈጠር ነው። ክሩ ተተርትሮና ተበጣጥሶ ከባድ ነፋስ ካለበት ቦታ በየመልኩ ከተከመረ በኋላ (ቤቱ ከፈረሰ በኋላ) መልሶ መሥራቱ ቀላል አይደለም፣ ምናልባትም አይቻል ይሆናል። ሕንፃው

አፍራሾች ጣለበት እንጂ የደራሲው ደጋፊዎች እንደሚሉት ድንጋዮቹ ተፈንቅለውበት ዐውቆ አልፈረሰም::

ከዚህ በፊት ደጋግሜ እንደተናገርኩትና እንደጻፍኩት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በዘር መደራጀትን መቃወም አለበት:: በታምራት ላይኔ ምስለኔነት የተደራጀው ኢህዴን ሊሞት ሲያጣጥር የዛሬው ደራሲ ከእሱ ያረገዘውና አሜሪካን ሀገር ላይ “የአማራው ብሔራዊ አንድነት ድርጅት” የሚባል አዋላጅ የተገኘለት፥ ከዚያም ኢትዮፒያን ሪቢው ላይ አልጋ የተነጠፈለት ጥቍር ውሻ ሲሆን ሲሆን ሳይወለድ እንዲጨነግፍ ማድረግ ከተወለደም እንዳያድግ ወተት መንሣት የሀገር ወዳጅ ሁሉ ግዴታ ነው::